# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

የነሐሴ ፴

የቃሉ ትርጉሜ ስርወ ቃሉ ከርመ፣ ከረመ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጐድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። የክረምት ዘመን ከሰኔ ፳፫ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ወሐመልማለ ለቅኔ እጓለ እመህያው
ዘይሁቦሙ ሲሳዮሙ ለእንስሳ
ወለዕጕለ ቋዓት እለ ይጼውዕዎ

ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም
ሣርን ለእንስሳ ያበቅላል
ለሚጠሩትም የቋዓት ልጆች
መዝ ፩፻፵፫፥፳-፬

ወንጌል፥ ሉቃ ፲፪፥፲፫-፳፫
ቅዳሴ፥ የአትናቴዎስ

| የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ |
|---|
| ሰንበት ተአቢ እምኵሉ ዕለት<br>«ከዕለታት ሁሉ ሰንበት ትበልጣለች» |

**በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች**

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፭፥፳-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕ ፪፥፲፬-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፭፥፩-፬ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### የሰበሰብከው ለማን ይሆናል?

ስናስቀድስ በሰማነው ወንጌል (ሉቃ ፲፪፥፲፫-፳፩) የተመሰለው ምሳሌ መነሻ ከዚሁ ምዕራፍና ቁጥር ፲፫-፲፭ የተጠቀሰው የክርስቶስን በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አይቶ እና አውቆ ለሥጋ ጥቅም የክርስቶስን ተወዳጅነት፣ ተቀባይነት በማዋል ከወንድሙ የእርሻ መሬት ለማግኘት የጠየቀው የሥጋ ጥያቄ ነው። ክርስቶስም መሬት ሊያከፋፍሉ የተሾሙ እንዳሉና ለዚህ ግን እርሱ አለመምጣቱን ጠቆመው (ቁጥር ፲፬)። የዚህ ሰው ለገንዘብ ብሎ ወንድሙን መክሰስና ፍቅር ማጣት፣ እንዲሁም የመክበር ፍላጐት ላይ የተመሰረቱ ምሳሌያዊ ትምህርት ከመስጠቱ በፊት ለምሳሌው መሰረት የሚሆን ቃል «የሰው ሕይወት በገንዘብ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ከመጐምጀት ሁሉ ተጠበቁ» በማለት ተናገረ። ከዚህ በማያያዝ ነበር ቀጣዩን ምሳሌ የመሰለው።

ምሳሌው፥
አንድ ባለጠጋ ሰው ነበር፤ እርሻው እጅግ ፍሬያማ ሆነችለት፣ ነገር ግን ለምርቱ ማከማቻ የሚሆን መዝገብ (ጐተራ) የለኝም በመሆኑም ያለኝን አነስተኛ ጐተራ አፍርሼ ትልቅ እሠራና በረከቴን አዲሱንና የከረመውን አነባብሬ አስቀምጣለሁ፤ ከዚያ በኋላ ነፍሴን «አንቺ ነፍሴ ለብዙ ዘመን የሚሆን ብዙ በረከት አለሽ እረፊ፣ ብዪ፣ ጠጪ፣ ደስም ያበልሽ እላታለሁ» አለ። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ነፍስህን ሊወስዷት የሞት መላእክት ይፈልጓታል፤ አንተም ዛሬ ትሞታለህ የሰበሰብከው ለማን ይሆናል አለው ይላል ምሳሌው። ጌታም ምሳሌውን ሲያጠቃልል በእግዚአብሔር ፈቃድ የማይሄድ ለራሱም ገንዘብ የሚያከማች እንዲህ ይሆናል አለ።

አንባቢ ሆይ፥ ከላይ የተጠቀሰው ታሪክና ምሳሌ ዛሬ ላለነው ሰዎች አስደንጋጭ አይደለምን? በእውነት ነው ምክንያቱም ዛሬ ሁላችንም ስለነገ የምንጨነቅ ይህን እንደዚህ፣ ያንንም እንደዚያ አድርገው፣ አልፎልኝ እኖራለሁ በማለት ያለ እግዚአብሔር ብቻችንን የነገውን ፕሮግራም የምንነድፍ ዛሬ ስላለንበት ሁኔታ ጌታን ማመስገን የማይሆንልን ነን። ይህ ባለጸጋ በሐሳቡ ጐተራውን ሲያፈርስ፣ የበለጠ ጐተራ ሲሰራ፣ በትልቅ ጐተራው ምርት ሲያከማች

## የሰበሰብከው ለማን ይሆናል? ...

ለሚቀጥሉት ረጅም ዓመታትም አርፎና ተዘልሎ ሲበላ፣ ሲጠጣ እንደሚኖር ተስፋ አደረገ። ነገር ግን ከነገም ሳይደርስ ምርቱንም ሳያከማች የጐተራውንም (በትንሽ ባልፈረሰችው ጐተራ ያለውን) ሳይበላው የዛሬውን ሕይወቱንም በምኞት እና በጭንቀት ወጥሮ አሳለፈው። እርሱም የዘራውን ሳይሰበስብ የሰበሰበውንም ሳይበላው ሞተ። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ረስቷልና ነው። ቅዱስ ያዕቆብ ሲመክር «ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን፣ እንነግድማለን፣ እናተርፋለን የምትሉ እናንተ ተመልከቱ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና ሕይወታችሁ ምንድን ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ በኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና። በዚህ ፈንታ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።» ይላል (ያዕ ፬፥፲፫-፲፭)። ሐዋርያው የሚለን አታስቡ፣ አታቅዱ አይደለም የሚለው «በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ ሁኑ» እንጂ (ሉቃ ፲፪፥፳፩)።

ሁላችንም በሥራችን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልንጠይቅ መግቦቱንም ልንረዳ ይገባናል። ጌታችን ስለ መግቦቱ በሰፊው ባስተማረበት ምዕራፍ «ለነገ አትጨነቁ» ብሏል (ማቴ ፮፥፴፬)። ምክንያቱም ለቀኑ ክፋቱ ስለሚበቃው ነው፤ ስለ ነገ ታስባላችሁ ዛሬን የመገባችሁ ነገም አለማለቱ ነው።

በብሉይ ኪዳን አንድ ታሪክ አለ፤ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲሄዱ ራባቸውና እግዚአብሔር መና አወረደ፣ መገባቸው ሲመግባቸው ከሰማይ የወረደውን መና ሲሰበስቡ ለዕለቱ የሚመገበውን ያህል ብቻ ይሰብስብ እንጂ ትርፍ አይሰብስብ፣ በየዕለቱ እመግባችኋለሁ አለ። ጌታችን ከእስራኤል ሕዝብ ግን አንዳንዶቹ በመሰሰት ከሚበሉት በላይ ሰበሰቡ፣ ሌሎቹ ደግሞ «ነገ እግዚአብሔር ቢያቆምስ ባይመግበንስ?» ብለው ነበር። ብዙ የሰበሰቡትም ሳያተርፉ ጨረሱት። ጥቂት የሰበሰቡትም አልጐደላቸውም ነበር። (ዘጸ ፲፮ በሙሉ)።

ዛሬም እኛ ከእግዚአብሔር ማዕድ የምንርቅ አምላክን ወረተኛ የምናስመስል የዛሬ ቸርነቱ ለዘለዓለም በእኛ ላይ ጸንቶ እንደሚኖር የማናምን መሆን የለብንም። ለራሳችን እራሳችንን ብቻ አናቅርብ «ከራስ በላይ ንፋስ ነው» ሳይሆን «ከራስ በላይ እግዚአብሔር ነው» እንበል። የሚያስጨንቀንን ሁሉ በእርሱ ላይ እንጣለው (፩ኛ ጴጥ ፭፥፯)፤ እንደ ባለቅኔውም «እመርዕስየ ለርዕስየ አንተ ትቀርቦ» እንበል አባባሉም ሲፈታ «ከራሴ ይልቅ ለራሴ አንተ ትቀርበዋለህ» ማለቱ ነው።

በእውነቱ ከእኛ ይልቅ አባታችን ስለ እኛ ያስባል። ክብር ለእርሱ ይሁን። አሜን።